## ምዝገባ ቀላል ነው!

በስልክ ለማመልከት ከሰኞ እስከ ዓርብ ከ 8 ኤኤም እስከ 7 ፒኤም ወይ ቅዳሜ 9 ኤኤም እስከ ከሰዓት በነፃ መስመር 1-833-522-5582 ይደውሉ( TTY መስማት ለተሳናቸው ወይ ለመስማት ለሚቸገሩ፡ 1-888-221-1590). አስተርጓሚዎች ተዘጋጅተዋል፡፡

ኦንላይን ለማመልከት commonhelp.virginia.gov ይጎብኙ፡፡ በተጨማሪም በአካባቢዎ በሚገኘው ማህበራዊ አገልግሎት ክፍል ማመልከት ይችላሉ፡፡

ሲያመለክቱ የቤተሰቦን ገቢ ኤሌትሮኒካዊ በሆነ መንገድ ለማረጋገጥ እንሞክራለን፡፡ በዚህ ስኬታማ ካልሆንን የገቢ ማረጋገጫ እንጠይቆታለን (የክፍያ ደረሰኝ ወይ ከአሰሪዎ ደብዳቤ)፡፡

የልጅልጆች ወይ የዘመድ ልጆች እያሳሰደጉም ከሆነ ለ FAMIS ማመልከት ይችላሉ፡፡

## >በተጨማሪም FAMIS ተብሎ የሚጠራ የድጋፍ ፕሪምየም አለ ይምረጡ እንዲሁም HIPP ለልጆች

ልጆቾ በ FAMIS ከተመዘገቡ፣ FAMIS ይምረጡ
ፕሮግራሙ ከአሰሪዎች የጤና እቅድና
FAMIS እንዲመርጡ
ይፈቅዳል፡፡ FAMIS ሰሌክት የአሰሪዎች የጤና መድህን ለሚመርጡ ወላጆች የልጆቹን የፕሪምየም መጠን ለመሸፈን ለአንድ ልጅ $100፣
በወር
ይሰጣል፡፡ **ነገር ግን መጀመርያ ማመልከትና ለ FAMIS መመዝገብ ይኖርቦታል፡፡**

የጤና መድህን ፕሪምየም ክፍያ (HIPP)
የልጆች ፕሮግራም ዕድሚያቸው ከ19 በታች ለሆኑና በሜዲኬድ ለተመዘገቡ ህፃናት የሚቀርብ ፕሪምየም ድጋፍ ነው፡፡ ብቁ ለሆኑ
ህፃናት
ወይ ብቁ የአሰሪ ስፖንሰር ሽፋን ለተመዘገቡና ለ
ሜዲኬድ፣ HIPP ብቁ ለሆኑ በከፊል ወይ ሁሉም የጤና መድህን ለመክፈል ድጋፍ ሊያደርግሎት ይችላል፡፡

ስለ ፕሪምየም ድጋፍ ፕሮግራም ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት
coverva.org ይጎብኙ፡፡

FAMIS
ያለምንም ክፍያ ልጆቾን ጥራቱን
የጠበቀ መድህን ሽፋን መስጠት

**1-833-522- 5582።**
**ወይ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት**
**coverva.org ይጎብኙ፡፡**

**Se habla español.**

TTY ለመስማት ለተሳናቸው ወይ መስማት
የተቸገሩ፡
**1-888-221- 1590።**

FAMIS የቨርጂንያ ኮመንዌልዝ FAMIS-4 0223 AM ፕርግራም ነው

# ጥራት
# የጤና መድህን
# ለህፃናት



# FAMIS

**ክትትሎች፡፡ የመድህኒት ትእዛዝ፡፡**
**የጥርስና የዓይን ህክምና፡፡**
**የአእምሮ ጤና እንክብካቤና ሌሎች፡፡**

COVER VIRGINIA
Connecting Virginians to Affordable Health Insurance
**coverva.org 1-833-5CALLVA**

# FAMIS የቨርጂንያ የህፃናት ጤና መድህን ፕሮግራም

## FAMIS ወይ ሜዲኬድ ለልጆቾ ትክክለኛ እቅድ መሆኑን ያረጋግጡ

FAMIS መድህን ለሌላቸው ህፃናት የሚቀርብ የቨርጅንያ የጤና መድህን መርሀግብር ነው፡፡ FAMIS እና ሜዲኬር ጥራቱን የጠበቀ የጤና እንክብካቤ ለህፃናት ያቀርባል፡፡ በቤተሰብ ቁጥርና ገቢ መሰረት ልጆቾ ብቁ ከሆኑ በ FAMIS ወይ ሜዲኬር ይመዘገባሉ፡፡

FAMIS እና ሜዲኬድ የልጆችን ጤና ለመጠበቅ የሚያስፈልጋቸውን መደበኛ የእንክብካቤ አገልግሎቶችና በተጨማሪም ከተጎዱ ወይ ከታመሙ በፍጥነት እንዲሻላቸው የሚረዳ አገልግሎቶችን ይሸፍናል፡፡ እንዲሁም ከሁሉም የሚበልጠው የልጆቾን እቅድና ሀኪም መምረጥ ይችላሉ፡፡
FAMIS የግል መረጃዎን በሚስጥር ያስቀምጣል-እምንፈልገው የልጆቾን ጤና እንድትጠብቁ ማገዝ ነው፡፡ መረጃዎን ለስደተኞች ክፍል አናጋራም እንዲሁም በነዚህ ፕሮግራሞች መመዝገቦ ባሎት የስደተኝነት ሁኔታዎ ላይ ችግር አያስከትልም፡፡

## ያለ ምንም ወጪ ለልጆች ጥራቱን የጠበቀ መድህን የሚያቀርብ ነው

ከ FAMIS እና የልጆች ሜዲኬድ  ልጆት ለሚያገኙት የጤና አገልግሎት የመመዝገብያ ክፍያ፣ ወርሀዊ ክፍያ፣ ወይ የጋራ ክፍያ የለም፡፡

*ማስታወሻ፡ ኔቲቭ አሜሪካኖችና አላስካን ለማንኛውም አገልግሎት የጋራ ክፍያ የላቸውም፡፡*

## FAMIS ፕሮግራም የገቢ ገደብ* (ድምር ገቢ)

ለ FAMIS ወይ የህፃናት ሜዲኬድ ብቁ ለመሆን የቤተሰብ ገቢና የቤተሰብ ቁጥር ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ የቤተሰብ መጠን ለማወቅ በፌደራል ግብር ላይ የተካተቱትን ጨምሮ ያሉትን ሰዎች ይቁጠሩ፡፡ ግብር የማይከፍሉ ከሆነ በቤቶ ውስጥ ዕድሚያቸው ከ19 ዓመት በታች የሆኑትን ልጆቾንና እንጀራ ልጆቾን ይቁጠሩ፡፡ የልጆቹ ወይ እንጀራ ልጆቹ እናት፣ አባት ከሆኑ እራስዎን ያካቱ፡፡ ከዛ በመቀጠል ሚስት ወይ ባል ይጨምሩ፡፡ ለምሳሌ 2 ዕድሚያቸው ከ19 ዓመት በታች የሆኑ ልጆችና/ወይ እንጀራ ልጆች ካሎት እራስዎንና ባለቤቶን ጨምረው፣ የቤተሰብ ቁጥር 4 ነው፡፡ ብቁነቶ የምንወስነው ከግብርና ተቀናሽ በፊት ባለው ወርሀዊ ገቢ ነው፡፡ አሁን ያለው ወርሀዊ ገቢ ገደብ የቤተሰብ ቁጥራቸው 4 ለሆኑት $5,125 ነው፡፡

| የቤተሰብ መጠን | ወርሀዊ | ዓመታዊ |
|---|---|---|
| 1 | $2,491 | $29,889 |
| 2 | $3,369 | $40,426 |
| 3 | $4,247 | $50,963 |
| 4 | $5,125 | $61,500 |
| 5 | $6,004 | $72,037 |
| 6 | $6,882 | $82,574 |
| 7 | $7,760 | $93,111 |
| 8 | $8,638 | $103,648 |
| እያንዳንዱ ተጨማሪ የቤተሰብ አባል | $879 | $10,537 |

*ከጃንዋሪ 20 2023 ጀምሮ ተፈፃሚ የሚሆን የገቢ ገደብ በየጊዜው ስለሚቀየር አሁናዊ ዝርዝር ለማግኘት coverva.org ይጎብኙ፡፡

ድምር ገቢ የሚባለው ግብርነ ተቀናሽ ከመቀነሱ በፊት ነው፡፡

## ሽፋን የሚያካትተው

- ለህፃናት፣ ጨቅላ ህፃናትና ታዳጊዎች ዓመታዊ ምርመራ
- በሐኪም የታዘዙ መድሃኒቶች
- የዶክተር ጉብኝቶች
- መርፌዎች
- የጥርስ እንክብካቤ
- የዓይን እንክብካቤና መነፀር
- የአዕምሮ ጤና እንክብካቤ
- ምርመራዎች እና ራጅ
- የሆስፒታል ቆይታዎች
- የድንገተኛ ክፍል እንክብካቤ
- እንዲሁም ተጨማሪ....

**በተጨማሪም በሜዲኬድ ውስጥ ለተመዘገቡ ህፃናት፡**

- መጓጓዣ ወደ ህክምና ቀጠሮ
- ልዩ የጤና እንክብካቤ ለሚያስፈልጋቸው ህፃናት ልዩ ህክምናና አገልግሎት

## ልጆት ብቁ መሆኑን ማረጋገጥ ያለበት

**ለ FAMIS  ወይ የልጆች ሜዲኬር ብቁ ለመሆን ልጅዎት መሆን ያለበት፡**

- በቨርጂኒያ ውስጥ የሚኖሩ
- ዕድሜው ከ19 በታች መሆን
- የዩናይትድ ስቴት ዜጋ ወይ ህጋዊ ፈቃድ ያለው ስደተኛ (የወላጆች የስደተኝነት ሁኔታ ግምት ውስጥ አይገባም)
- የቤተሰብ ገቢ (ግብርና ተቀናሾች ከመቀነሱ በፊት) በ FAMIS ገደብ መሰረት (ቻርቱን ይመልከቱ)

**FAMIS ብቻ፡**

- በሚያመለክቱበት ግዜ ልጆቾ መድህን ሽፋን ሊኖራቸው አይገባም

**በጣም ቀላል የስክሪን መጠቀምያ መሳርያ ለማግኘት coverva.org ይጎብኙ፡፡**

**ለህፃናት ጥራቱን የጠበቀ የጤና መድህን**